# ይድረስ ለጀርመን ድምፅ ዐማርኛ አግልግሎት

<u>ቦን/ጀርመን</u>

በተቀዳሚ የከበረ ሰላምታችን ለሁላችሁም ይድረሳችሁ። በዘገይም እንኳ ለአዲሱ ዓመት ዘመነ ማቴዎስ 2013 ዓ.ም በሰላም በጤና አሸጋገራችሁ።

በመቀጠልም እ.አአ 29/09/2020 ባቀረባችሁት ዝግጅት <<ዐማርኛ ከእንግሊዘኛ ጋራ የመቀየጥ አባዜ>> በተሰኝ ርእስ በወይዘሮ አዜብ ታደስ መሪ አዋዋይነት የተደረገውን ጠቃሚና አስደማሚ ቅንብር አድምጠናል። በመሆኑም ለወይዘሮ አዜብ በጣም የጠለቀ ሙያዊ አቀራረብና ችግሩን ከሁሉም አቅጣጭያ አገናዝቦ የማቅረብ ክህሎት ከፈተኛ ምስጋ እናቀርባለን።

አዎ! በዐማርኛ ቋንቋ ላይ የሚደረገው ዘመቻ እጅግ በጣም ዘርፈ ብዙ ነው። በቀረበው ዝግጅት በከፊል ብቻ ነው የተገለጸው። በተለይም ከአለፉት 30 ዓመታት ጀምሮ በከተማዎች እንደ አዲስ አበባና ያማራ ክልል ተብዬዎቹ እንደ ባሕር ዳር፣ ጎንደርና ደሴ ባሉት ዐማርኛ ሞቶ ተቀብሯል።

አብሶም በባሕርዳርና ጎንደር ከተማ ያሉት ነዋሪዎች የጣና ሐይቅን በመጤ ወራሪ እንቦጭ አረምና በጣም ስግብግብ ትርፍ አግበስባሽ ጥቂት ሃብታሞችና ብዙኀን ደናቁርት ምስኪኖች በሚጥሉት ቆሻሻና ውዳቂ ፍሳሽ አስቀድሞ ከአፍሪቃ አህጉር ንጹሕና ያካባቢው ሥነ ምኀዳር ያልተበከለ የነበረውን ጣና ሐይቅን እንደበከሉትና በመጥፋት ሂደት እንደሚገኘው ሁሉ ያማርኛንም ቋንቋ ከእንግሊዘኛ ጋራ እየዘነቁ ሲንበላጠጡና ሲጨማለቁ ይስተውላሉ። ከዝነቃውም ሌላ ያማርኛን ግስ (አንቀጽ) ርባታ ደንብና ሕግ አፋልሰው፣ ጥሰውና አዘበራርቀው ይፎልላሉ። ለምሳሌም በላሁኝ፣ ጠጣሁኝ፣ ሠራሁኝ፣ መጣሁኝ. ወዘተ. እያሉ ዐማርኛ ብለው ሲናገሩ መስማት በጣም ይቀፋል። እኔ ለተባለው ምድብ ተውላጠ ስም መድረሻ ዝርዝሩ -ሁ፣ -ኹ እና -ኩ ናቸው እንጅ -ኝ ፈጽሞ መግባት የለበትም። በግእዝም ቢሆን ተመሳሳይ ነው። በላዕኩ፣ ሰገድኩ፣ መጻእኩ ባማርኛ በላኹ፣ ሰገድኹ፣ መጣኹ ተብሎ ነው አንቀጹ የሚራባው።

አንድ የደቡብ ኢትዮጵያ አዋሳ ከተማ ነዋሪ መምህር ወደ ባሕርዳር ሄደው የገጠማቸውን ሁኔታ ባለፈው ዓመት በሰፊው አሳውቀውናል። የባሕርዳር ጭራቀረሽ ነዋሪዎች እንግሊዘኛን እየዘነቁ ሲያሽቃብጡ ተመልክተው ተመልሰዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ ደግሞ ዐማርኛን አስመልክቶ በዘመነ ወያኔ ትግሬ ሕወሓት እንዴት እንደነበር ምስጋና ለጀርመን ድምፅ በማንተጋፍቶት ስለሽ አቅራቢነት ተዘጋጅቶ ባለፈው ዓመት የቀረበልንን ከቶ አንዘነጋውም። በዚህም ረገድ በአዲስ አበባ የግል ትምህርት ቤቶች ሕፃናት በቋንቋቸው ባማርኛ ሲናገሩ ይቀጡ እንደነበር ታውቋል። እረ! ምን ይህስ ብቻ "ዐማርኛ መናገርና ድንጋይ መወርወር ክልክል ነው" ማስታወቂያ በሰሌዳ ላይ ለጥፈው እንደ ነበርም ተዘግቧል። የንግድ ድርጅቶች፣ ሆቴሎችና ልዩ ልዩ ተቋሞች ሁሉ ያማርኛን ፊደልና ጽሑፍ ተጸይፈው አውቆ ፈረንጅ ለመሆንና ለመምሰል ያላደረጉት ከተ ምን አለ?

ከለይ የተገለጹት ሁኔታዎች የዚህን አፋሽ አጎንባሽ፣ በጣም ወራዳ ወፍዘራሽ ውዳቂ ትውልድ ልዩ መገለጭያው መሆኑን ፍንትው አድርጎ ያሳያል።

የኢትዮጵያ ልሂቃን ተብዬዎቹ ዐማርኛን ከእንግሊዘኛ ጋራ የመዘነቅ አባዜ የተጠናወታቸው ስለ ሁለት ምክንያቶች እንደሆነ እናሰምርበታለን።

፩ኛ ያስኮላው ዘመናዊ ትምህርት ቤት ውጤት ልሂቃን ነኝ ባዩ ያማርኛን ቋንቋ ፈጽሞ፣ አይችሉትም። እንኳን መዝገበ ቃላቱን ይቅርና ፊደልና የአጻጻፍ ደንብና ሥርዓቱን በጭራሽ አያውቁትም። ያማርኛ ቋንቋ ከጀርመንኛ፣ ከእንግሊዘኛ፣ ከፈረንሳይኛ፣ ከእስጳኝ፣ ከአረቢ፣ ከእብራይስጥ ከሕንዲ. ወዘተረፈ የበለጠ ቃላት አሉት። በዓለም ላይ እንዳሚገኙት እንደማንኛውም ቋንቋ አዳዲስ ዘመናዊ የቃላት አሰያየም ሥርዓትና ደንብ አለው። ነገር ግን ልሂቅ ተብዬው ከጥቂት ተዘውትሮ ከሚሰማው ቃላት በስተቀር ምንም ነገር አያውቅም። ታዲያ! አለማወቁን ታዲያ! አለማወቁን ለመሸፈን ሲል ነው ያማርኛ መዝገበ ቃል ጭራሽ እንደሌለ አድርጎ የእንግሊዘኛ ቃል ዘንቆ ሐር አምባና ቆቦ የሚቀባጥረውና የሚያወናብደው።

የእንግሊዘኛ ቋንቋንም ቢሆን አስተካክሎ የሚናገር ልሂቅ ተብዬ በጣት ይቆጠራል። ስለምን ቢባል በኢትዮጵያ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት መልስ ክፍተኛ ትምህርት በእንግሊዘኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት መሰጠት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ተማሪው ፈጽሞ በማይገባው፣ እቤቱ ውስጥ ሆነ በአካባቢው በማይገለገልበት፣ ጠንቅቆ በማያውቀውና በማይረዳው፤ ወላጅ እንዲሁም አስተማሪዎች በሆኑ ፈጽሞ በማይገባው የእንግሊዘኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት የትምህርቱ ይዘትና ጥልቀት ለተማሪው ሳይገባው የቃል ጥናቱን ብቻ በቃል እያነበነበ ዓመታት አስቆጥሮ የወጣትነት ጊዜው በከንቱ ያልፋል። ሥርዓተ ትምህርቱ የተዘጋጀው ልክ እንደ ጥንቱ የቤተ ክህነት ትምህርት ቤት ቃል በቃል ሸምደዳ ሆኖ እስከ ዛሬም ዘልቋል። በራስ ቋንቋ መማርና ማስተማር ለአንድ አገር እድገትና ርምጃ ዋና ቁልፍ መሆኑ እየታወቀ፣ በአገራችን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት መልስ ለእንግሊዝ ተስፋፊዎች ሴራና ደባ እጅ ተሰጥቶ ለውድቀትና ኋላ ቀርነት ዋናው ምክንያት መሆኑን ከቶ መዘንጋት የለበትም። በራስ ቋንቋ የተዘጋጁ ጽሑፎችንና የሙያ መጻሕፍትን በቀላሉ አንብቦ ለመረዳት ይቻላል። የመማር ማስተማሩም ተግባር ቀላል መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ሐቀ ነው። ስለሆነም ነው በአውሮፓ ትንንሽ ይሁኑ ወይም ትልልቅ አገሮች ትምሕርትን ለሕፃናቶቻቸው ከመዋዕለ ሕፃናት እስከ የኒቨርስቲ በየራሳቸው ቋንቋ የሚያስተምሩት። ለምሳሌ ጃፓን ከምዕራቡ ዓለም ሳይንስና ቴክኖሎጅ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ወስዳ ከራሷ ቋንቋ ጋራ የተስማማ ሥርዓተ ትምህርት አዘጋጅታ በማስተማርዋ ምክንያት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ርምጃ ለማድረግ ችላለች። ከጃፓንም ሌላ በቅርቡ የኮሪያ፣ የቻይና፣ የእሥራኤል ወዘተረፈ ሕዝቦች ሁሉ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ከፍተኛ ርምጃ ያደረጉት ወጣቶቻቸውን በየራሳቸው ቋንቋ ስለሚያስተምሩ ነው። በአንጻሩ ኢትዮጵያና የአፍሪቃ ነፃ ተብዬ አገሮች ግን የፈረንሳይና እንግሊዝ የቋንቋና ባሕል ኢምፔሪያሊዝም መፈንጪያ ሆነው የወደፊት ሳይሆን የኋሊት ጉዞ ጀምረዋል።

፪ኛ ያማርኛ ቋንቋ ከዛጉዌ ሥርዎ መንግሥት ጀምሮ ልሳነ ንጉሥ ተብሎ እስከ ዛሬ ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥትና ልዩ ልዩ ነገዶች የጋራ መግባቢያ የጽሑፍ ቋንቋ ነው። ኢትዮጵያን ልዩ አገር በዓለም ላይ የሚያስደርጋት የራሷ ፊደልና ሥነ ጽሑፍ ሥልጣኔ ያላት ነፃና ጥንታዊት አገር መሆኗ በተቀዳሚ ይገለጻል። ያውሮፓ ቅኝገዥ ተስፋፊዎች አፍሪቃን ተቀራምተው ቋንቋቸውን እንዳስፋፉት በኢትዮጵያ ግን ሞክረው አልተሳካላቸውም። ስለሆነም ነው ባማራው ሕዝበ ክርስቲያንና ባማርኛ ቋንቋ ላይ የጥላቻ ቅስቀሳና ዘመቻ ከአድዋ ድል መልስ በስውርና በግልጽ ሲነዙ የኖሩትና ያሉት። ኢትዮጵያ በአርበኞችዋ የአምስት ዓመታት ተጋድሎ የፋሽስት ጣሊያንን አረመኔያዊ ፍጅትና እልቂት ድባቅ መታ ነፃነቷን ስታረጋግጥ ከምንም ተነስታ በአጤ ኃይለ ሥላሴ መሪነት ከፍተኛ ርምጃ አድርጋለች። በትምህርት መስከ ዘመናዊው ትምህርት ከሦስተኛ ክፍል ጀምሮ እስከ ዩኒቨርስቲ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ልክ እንድ እንግሊዝ ቅኝ ተገዥ አገራት ሲሰጥ ነበር። ያማርኛ ቋንቋ እንደ አንድ ክፍለ ትምህርት ቢሰጥም እንኳ በዚያን ጊዜ ማስተማሪያ መጻሕፍት አልነበሩም። ቀጥሎም በአሜሪካኖች አማካሪነት እስከ ስድስተኛ ክፍል ድረስ ባማርኛ ማስተማር ተጀመረ። ያማርኛ ቋንቋ አካዴሚ የተሰኛ ድርጅት በአጤው ዘመነ መንግሥት ማክተሚያ ዋዜማ ተመሥርቶ ነበር። ወታደራዊ ደርግ ሥልጣን ሲይዝ አካዳሚው የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ኢንስቲትዩት ተባላ። የኢትዮጵያ ተማሪዎች በአውሮፓና ሰሜን አሜሪካ የነበሩትና በአገር ቤት አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በተሰኘው የነበሩት ግልገል ፋሽስቶች "የብሔር የራስን እድል በራስ መወስን እስከ መገንጠል መበት" እያሉ ዐማራውን ሕዝብ ለይተው "ጨቋኝ" ሌላውን ነገድ በጅምላ "ተጨቋኝ" እያሉ በከፍተኛ ፖለቲካዊ ትግል ተመልሳ የተዋሃደችውን ኤርትራን ለማስገንጠል ታስቦና ታቅዶ እኮ ነበር ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ሲነዜ የነበረው። ያማርኛና ያማራ ሕዝብ ጥላቻውም በቅጥረኛ ባንዳ ውላጆቹ እነ ሻዕቢያ፣ ትሕነግ እና ኦነግ ጉጀሌዎች ዘንድ በጣም ሥር የሰደደና የተስፋፋ ነው። አስቀድሞም የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ማኅበር መገልገያ ቋንቋ እንግሊዘኛ ሆኖ ጥቂት የትግሬና የወረሞ ጠባባ ብሔረተኞችና አብዩታዊ በቀቀኖች ሲኮላተፉ እንደ ነበር አይተናል ሰምተናል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከምልምል ግልገል ፋሽስት ተማሪዎቹም ሌላ የቋንቋ አስተማሪ ተብዬዎቹም ባማርኛና በፊደሉ ላይ የጥፋት ዘመቻቸውን በተለይ በዘመነ ወያኔ ትግሬ ሕወሓት አድርገዋል። ያማርኛ ሞግሼ ፊደላትን አሶግደዋል። እነዚህ የኢትዮጵያን ፊደል ምንነት ታሪክና እድገት አጣርተው ባለማወቃቸው ኅፍረተቢስ የሆኑ ዝንጅሮዎች፣ ዐይናቸውን በጨው ያጠቡት ቀጣሪ መልማይ ፈረንጅ አስተማሪዎቻቸው የሚነግራቸውን ሁሉ ተጭነውና በቀጥታ ያለማገናዘብ ተከትለው <u>ፊደሉ በዛ</u> ፣ ልክ እንደ ሮማይስጥና ጽርዕ ፩አ፣ ፩ሀ፣ ፩ሠ፣ ፩ጸ ብቻ ይበቃል ብለው አመሳቃቅለዋል። በአንደኛው ማለትም በግእዙ አ እና በራብዕ ኣ መካከል ያለውን የድምፅ ልዩነት እንኳ ሳይለዩ ነው፣ እንደ ዐማርኛና የግእዝ ቋንቋ ደንብ ሥርዓት ሳይሆን ጉረሮ ሞራጅ እንደ ሆኑት ትግርኛ፣ ትግረ እና አረቢ በአፍ አስከፋቹ የራብዕ ፊደል ድምፅ ለምሳሌ ኣማራ ኣማርኛ ወዘተ. እያሉ ጽፈዋል፣ አሳትመዋል። ይህ ፈጽሞ ስሕተት ነው። ዐማራ፣ ዐማርኛ ተብሎ መጻፍ ነው ያለበት። ዐማራ የሚለውም መጠሪያ ስም ከሁለት ቃላት ዐም እና ሐራ ይወጣል። ዐም ማለት ሕዝብ + ሐራ ነጻ ዐማራ ነፃ ሕዝብ ተብሎ ነው የሚተረጎመው።

በመጀመሪያ ደረጃ ያማርኛና ግእዝ ሞግሼ ፊደላት ስማቸው እንጂ ቅርፅና ትርጉማቸው የተለያየ ነው። ታላቁ ምሑር ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ እንደገለጹት የኢትዮ፝ያ ፊደል ተራውና ቅርፁ እያንዳንድ ጥልቅ ምሥጥርና ቋሚ ትርጓሚ ስላለው መፋለስም ሆነ መቀነስ የለበትም። ደግሞስ በፊደል ቅርፅ መመሳሰል ችግር ቢባል እንደ አረቢ እና እብራይስጥ ያሉትን መጥቀስ ይቻላል። የኛ ፊደል እንኳን ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ይቅርና በዓለም ላይ ሳሉት ቋንቋዎች ሁሉ መጻፊያነት እጅግ በጣም ተስማሚና አመቺ ነው። ፊደላችን ሁሉም እንደተጻፉ ይነበባሉ። በሌላ በኩል እንግሊዘኛ ከኛው ጥንታዊ መነሻ ፊደላት በተወሰደው ግሪክና ላቲን ተብዬው ፊደል ልጻፍ ብሎ ዝብርቅርቁ ወጥቷል። አንዱ ፊደል የተለያየ ድምፅ አለው። ያንድን ቃል ፊደላትና አነባብ ተናጋሪው ካልሸመደደ መናገርም መጻፍም አይችልም።

፫ኛ
ዐማርኛን ከእንግሊዘኛ ጋራ እየዘነቁ ከሚናገሩትም ሌላ ያማርኛን የፊደል ትክክለኛ አገባብ የማይችሉት መሐይማን ሞልተዋል። ያማርኛን ግስ (አንቀጽ) ምንጭ ባለማወቃቸው ነው የነ አዐ፣ ሀሐኀ፣ ሠሰ፣ ጸፀ ፊደላትን አዛንቀው የሚጽፉት። ለምሳሌም ያህል፤

ባሕር ዳር በማለት ባህር ዳር፤ ማኅበር በማለት ፈንታ ማህበር
መንግሥት በማለት ፈንታ መንግስት፤ ሕዝብ በማለት ፈንታ ህዝብ
ብሔር በማለት ፈንታ ብሄር፤ ሃይማኖት በማለት ፈንታ ሐይማኖት
ሰላም በማለት ፈንታ ሠላም፤ ብርሃን በማለት ፈንታ ብርሐን
ኃይል በማለት ፈንታ ሃይል፤ ዐዲስ በማለት ፈንታ አዲስ
ዐጤ በማለት ፈንታ አጤ፤ ዐይን በማለት ፈንታ አይን
ዓለም በማለት ፈንታ አለም፤ ዕፅ በማለት ፈንታ እጽ፣ ወዘተረፈ.


እነ ተፈረደኝ ኃይሌ /ዶክተር የኬሚካል መሃንዲስ
የውብዳር ዘለቅ /ዶክተር የሥነ ልሳን
ገብሬ ጉልቱ /ዶክተር የሥነ ልሳን
አቶ ገሞራው ማንያዘዋል የሥነ መረጃ ቴክንሎጂ ባለሙያ ከታቢ
ወይዘሮ ደብሪቱ አጎናፍር የሥነ ምጣኔ ሃብት

ከኢትዮጵያዊ ዐማራ ሕዝብ ድርጅት (ኢዐሕድ) የአውሮፓው ዘርፍ
aeapo49@gmail.com


መስከረም 23 ቀን 2013 ዓ.ም